# ማውጫ

መግቢያ....1
ዋና ዋና የተግባራት አፈፃፀም....3
1. መከላከል....3
1.1. የመረጃና ትምህርት ስርፀት....3
**1.1.1.** የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት....3
**1.1.2.** መረጃ ትምህርትና ስርፀት ቁሳቁስ....4
**1.2.** የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት ት....6
**1.3.** ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል....9
**1.4.** የኮንዶም ትውውቅና ሥርጭት....11
**1.5.** የአባላዘር በሽታዎችን መከላከልና ማከም....11
**1.6.** የማህበረሰብ ውይይት....12
**1.7.** ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተከናወኑ ተግባራት....16
**2.** ድጋፍና ክብካቤ....0
**2.1.** ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝና የኤድስ ህሙማን ድጋፍና የማህበራት እንቅስቃሴ....18
*2.2. ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች የሚደረግ ድጋፍ*....20
**2.3.** የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት አገልግሎት....22
3. የአቅም ግንባታ....23
**4.** የሰው ሃይልና ሌሎች የአስተዳደር ዘርፍ ስራዎች....31
**5.** የክትትልና ድጋፍ ተግባራት....33
**6.** የበጀት አጠቃቀምና በፋይናንስ ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት....35
**7.** ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች....35
**7.1** ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች....37
**7.2** የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች....38
**8.** የታዩ መልካም የስራ እቅስቃሴዎች....38
**9.** ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች....39

# መግቢያ

በ2001 በጀት ዓመትም በክልሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት ለመግታት የሚደረገው ጥረት የበለጠ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ህብረተሰቡ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በባለቤትነትና በግንባር ቀደምነት እንዲሰለፍ እየተደረገ ነው፡፡

በክልላችን እየጨመረ የመጣውን የህብረተሰቡን የኤች.አይ.ቪ. የደም ምርመራ ፍላጎት ለማሟላትና የቫይረሱን ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ የመከላከል አገልግሎቶች የማስፋፋት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህም መሠረት ባለፈው አንድ ዓመት በመከላከሉ ዘርፍ ለ13,760,913 የህብረተሰብ ክፍሎች በልዩ ልዩ መንገዶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት፣ ለ **1,645,833** ሰዎች የኤች.አይ.ቪ. የደም ምርመራ እንዲሁም 98538 እናቶች ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ የመከላከል አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

የኤችአይቪ. ስርጭት ከመከላከል ጎን ለጎንም የፀረ-ኤች አይ ቪ. መድሃኒት ተጠቃሚውን ቁጥር ማሳደግ፣ የድጋፍና ክብካቤ ተግባራትን ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በበጀት ዓመቱ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህም መሠረት 23688 አዋቂ ሰዎችና ህፃናት የፀረ ኤች አይ ቪ. መድሃኒት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ አገልግሎቱም በ104 የመንግስት ጤና ተkማት ( 87 ጤና ጣቢያና 17 ሆስፒታሎች) እየተሰጠ ይገኛል፡፡

ኤችአይቪ. በደማቸው የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍሎች በማህበራት አማካኝነት የመሠረታዊ ፍላጐት፣ በገቢ ማስገኛ ተግባራት በመሰማራት ፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት መውሰድ ያለባቸው ያለማቋረጥ እንዲወስዱ ማበረታታት፣ በግንዛቤ ማዳበሪያና የህዝብ ንቅናቄ ተግባራት ተሳታፊ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡

የማህበረሰብ ውይይት በክልላችን ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር እንዲሁም ህብረተሰቡን ለልማት በማነሳሳት አቅሙን በማጎልበትና የባለቤትነት ስሜትን በመፍጠር ተጨባጭ የሆኑ ለውጦችን እያስገኘ ነው፡፡ ስለሆነም ባለፉት ዓመታት ውይይቱ በተጀመረባቸው እንዲሁም አዳዲስ ጣቢያዎች በክልሉ በሚገኙ *3426* ቀበሌዎች ውይይቱን ለማዳረስ የተቻለ ሲሆን በቀጣይነትም በቀበሌ ከአንድ በላይ የውይይት ጣቢያዎች ለማቋቋም እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱም እስካሁን በክልሉ የማህበረሰብ ውይይት የሚደረግባቸው

ጣቢያዎች ብዛት 4250 (3877 ቀበሌ ላይ እና 373 ት/ቤቶች ላይ) የደረሰ ሲሆን የውይይቱን ጥራት በማስጠበቅ የተሻለ ውጤት እንዲገኝ የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በበጀት ዓመቱ የሴክተር መ/ቤቶችን እንቅስቃሴ ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ በክልል ደረጃ የሚገኙ የሴክተር መ/ቤቶች ዓመታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ የቴክኒክ እገዛ ተደርጓል፡፡ በዞኖችና በወረዳዎችም ይሄው ተግባር እየተጠናከረ የሚገኝ ሲሆን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ በጀት መመደብ፣ የኤድስ ፈንድ ማቋቋምና ሌሎች የድጋፍና ክብካቤ ተግባራት እንዲፈፀሙ የማስተባበርና የቴክኒክ እገዛ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የመከላከልና መቆጣጠር ተግባራትን ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ የሰው ኃይልና ተቋማት አቅም ግንባታ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን በየደረጃው በርካታ ስልጠናዎች ለፈፃሚ አካላትና ለማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ተሰጥተዋል፡፡

ከማስተባበሩና ሃብት ማሰባሰቡ በተጨማሪም የሚካሄዱ ተግባራትን አፈፃፀም በየደረጃው የመከታተልና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ መደበኛ ተግባር ሆኖ እየተፈፀመ ይገኛል፡፡ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ክንውን አፈፃፀም በየደረጃው ለመገምገም የሚረዳ አሳታፊ ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡

# የዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም

## *1. መከላከል*

በ2001 በጀት ዓመት በዕቅድ ተይዘው በተለያዩ አካላት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የኤችአይቪን ስርጭት የመከላከል ሥራ አንዱና ዋነኛዉ ነው፡፡ ሕብረተሰቡም የኤች.አይ.ቪ. የምክርና የደም የምርመራ፣ ኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል፣ የፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት ተጠቃሚነትና የህክምና ባህሉን በማሳደግ በተለይም ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የበለጠ የሚያጋልጡ የአባላዘር በሽታዎችን ፈጥኖ የመታከም አገልግሎቶች ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም በኮንዶም አጠቃቀምና በሌሎችንም በርካታ መሻሻሎች ተገኝተዋል፡፡ በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ በመከላከሉ የነበረው ክንውን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1.1. የመረጃና ትምህርት ስርፀት

#### 1.1.1 የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት

ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስለበሽታው ምንነት፣ መተላለፊያና መከላከያ ዘዴዎች እንዲሁም ስለሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጫና ለሕብረተሰቡ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት በየጊዜዉ በተለያዩ መንገዶች እየተሰጠ ይገኛል፡፡

በ2001 የበጀት ዓመት የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለ 13,760,913 ሕዝብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሠጥቷል፡፡ የዕቅድ ክንውኑም 103 % ነው፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቱ በገጽ ለገጽ ገለፃ ዝግጅቶች፣ በሚነበቡ ቁሳቁሶችና በሚደመጡ መረጃዎች (ሚዲያ)፣ በስነ ጽሑፍ፣ በድራማና በግጥም፣ በአቻ ለአቻ ውይይት፣ በሚኒሚድያ፣ በማህበረሰብ ውይይት፣ በፓናል ውይይት፣ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ውስጥ ያለባቸው ሠዎች በሚሰጡት የምስክርነት ቃል፤ በእምነት ተቋማት፣ በት/ቤቶች፣ በገበያ ቦታዎችና በስብሰባ ቦታዎች ላይ ግንዛቤው እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡

በሐይማኖታዊና ህዝባዊ በዓላት ቀን ወቅታዊ መልዕክቶች እንዲተላለፉ ከተለያዩ አካላት ጋር በመሆን እንቅስቃሴ በማድረግ የአፈፃፀም መሻሻል እንዲኖር ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክልሉ ውስጥ የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች በሬዲዮ፣በቴሌቪዥን በጋዜጣ፣በኤፍኤምና በዜና ፕሮግራሞች በብዙሃን መገናኛ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የጥያቄና መልስ በኤፍኤም ተካሂዷል፤52 የተሸሉ ተሞክሮዎች፣40 የተለያዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች( 190

ደቂቃ)፣ 26 ሳምንታዊ የበኩር ጋዜጣ ትውልድ ይዳን የሚል መልዕክት የያዘ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

በክልል፣በዞን፣በወረዳና በቀበሌ የዓለም ኤድስ ቀንን ምክንያት በማድረግ የመንግት፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማህበራት የሐይማኖት ተቋመት ከፍተኛ የሆነ የቅስቀሳ ስራ አከናውነዋል፡፡

በ2001 የበጀት ዓመት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት በዞን ደረጃ

| ተ.ቁ | ዞን/ክልል | መለኪያ | የዓመት ዕቅድ | ክንውን | % |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ደቡብ ወሎ | ቁጥር | 1,644,480 | 1501795 | **91** |
| 2 | ሰ/ሸዋ | » | 1,000,**000** | **1515077** | **151.5** |
| 3 | ምስራቅ ጎጃም | » | 710,070 | 824496 | 116 |
| 4 | አዊ | » | ***980,505*** | ***1440713*** | ***147*** |
| 5 | ምዕራብ ጎጃም | » | ***3,128,936*** | ***2550847*** | ***81.5*** |
| 6 | ሰ/ጎንደር | » | **2600000** | 2505814 | 96.3 |
| 7 | ደቡብ ጎንደር | » | ***1,388,788*** | ***1042767*** | ***75*** |
| 8 | ሰ/ወሎ | » | ***910,005*** | ***738743*** | ***81*** |
| 9 | ዋግ ኽምራ | » | 431,000 | 555289 | 128.8 |
| 10 | ኦሮሚያ | » | ***514,400*** | ***454838*** | ***88.4*** |
| 11 | ባህር ዳር | » | ***45,000*** | ***49391*** | ***109.7*** |
| 12 | በክልል ቢሮዎችና ማህበራት | » | | **581143** | |
| | ድምር | | ***13353184*** | **13760913** | ***103*** |

**ማሳሰቢያ፡ በክልል ቢሮዎችና ማህበራት የተከናወነው የግንዛቤ ማስጨበጫ ት/ት በዕቅድ ውስጥ ያልተካተተ ነው፡፤**

### 1.1.2 የመረጃ ትምህርትና ስርፀት ቁሳቁስ

በተለያዩ የመረጃና ትምህርት ቁሳቁስ አማካኝነት ለሕብረተሰቡ ትምህርት መስጠት የባሕሪ ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል ለመቆጣጠር ድጋፍ፣ እንክብካቤና የህክምና አገልግሎት ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ቁልፍ ሚና አለው፡፡

በተለያዩ አካላት ተዘጋጅተው ለሕብረተሰቡ የሚሠራጩት የመረጃ ትምህርትና ስርፀት ቁሳቁሶች የሕብረተሰቡን የግንዛቤ ደረጃ ያገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት በበጀት ዓመቱ ከተሰራጩት የመረጃና ትምህርት ቁሳቁሶች መካከል በራሪ ጹሑፎች፣ ብሮሸሮች፣ ፖስተርና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ በክልልና በዞኖች በድምሩ 1,469,979 የተለያዩ የመረጃና ትምህርት ቁሳቁስ ስርጭት ተካሂዷል፡፡ ይህም የዕቅዱን 77.2 በመቶ አፈፃፀም ያሳያል፡፡

# የመረጃና ትምህርት ቁሳቀስ (ህትመቶች) ስርጭት በዓይነት

| ተቁ | ዞን /ወረዳ | መለኪ ያ | ዓመታዊ ዕቅድ | ክንውን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በራሪ ፅሁፍ | ብሮሸር | ፖስተር | መጽሔት | ካኔቴራና ኮፍያ | ሌሎች ህትመቶች | ድምር | % |
| 1 | ደቡብ ወሎ | ቁጥር | 117,016 | 94887 | 7404 | 259 | 488 | 1292 | 335 | 104665 | 89.4 |
| 2 | ሰ/ሸዋ | » | 220,480 | 39463 | 6956 | 7657 | 963 | 888 | 49473 | 105400 | 47.8 |
| 3 | ምስራቅ ጎጃም | » | 500,000 | | | 291 | | 810 | 186862 | 187963 | 37.6 |
| 4 | አዊ | » | 157,000 | 94458 | 6945 | 1741 | 77 | 80 | 12857 | 116088 | 73.9 |
| 5 | ምዕራብ ጎጃም | » | 200,000 | 145553 | | 1392 | 395 | 769 | 2113 | 149629 | 74.8 |
| 6 | ሰ/ጎንደር | » | 230,000 | | | | | | | 306912 | 133.4 |
| 7 | ደቡብ ጎንደር | » | 224,662 | | | | | 828 | 195072 | 195900 | 87.2 |
| 8 | ሰ/ወሎ | » | 73,620 | 37727 | 0 | 381 | 0 | 251 | 366 | 38725 | 52.6 |
| 9 | ዋግ ኽምራ | » | 26,000 | | | | | | | 20117 | 77 |
| 10 | ኦሮሚያ | » | 43500 | 12034 | 7400 | 3833 | 262 | 338 | 2404 | 19710 | 45.3 |
| 11 | ባህር ዳር ከተማ | » | 70,000 | 24354 | 19069 | 7022 | 823 | 3793 | 6108 | 61169 | 116.5 |
| 12 | በክልል ቢሮ | » | 40,414 | 87310 | 20000 | 39534 | 10000 | | 6857 | 68389 | 169 |
| | ድምር | | 1,902,692 | 535786 | 67774 | 62110 | 13008 | 9049 | 462447 | 1469979 | 77.2 |

* በክልሉ ውስጥ በአጠቃላይ 69 የቢል ቦርድ (ታፔላ) መልዕክቶች እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡

## የኤድስ መረጃ ማዕከላት

በአማራ ክልል ውስጥ ከብሔራዊ የኤድስ መረጃ ማዕከል ጋር በመተባበር በባህር ዳር፣ በደሴ፣ እና በጎንደር ከተሞች የኤድስ መረጃ ማዕከላት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

ማዕከላቱ በዋናነት ህብረተሰቡ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ተዛማጅ ጉዳዮች ጠቃሚ መረጃ በኢንተርኔት፣ በኦዲዮ ቪዥዋልና የህትመት ውጤቶች በማግኘት ግንዛቤውን እንዲያሳድግ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በተጨማሪም በመስኩ የሚደረጉ ጥናቶችን በማገዝ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በክልሉ የሚገኙት ሦስት የኤድስ መረጃ ማዕከላት በበጀት ዓመቱ ተጠቃሚዎችን በተዘረዘሩት አገልግሎቶች ያስተናገዱ ሲሆን 55829 ወንዶችና 2318 ሴቶች በድምሩ 58147 ሰዎች በመረጃ ማዕከሉ የተለያዩ መረጃዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ሴቶች በመረጃ ማዕከላት በብዛት ተጠቃሚ አለመሆናቸውን የተስተዋለ ሲሆን ወደፊት ትኩረት የሚያስፈልገው መሆኑን ያሳያል፡፡

### 1.1.3 የኤች.አይ.ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት

የኤችአይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት የኤች.አይ.ቪን ሥርጭት ባለበት ለመግታት ከኤች.አይ.ቪ ነፃ የሆኑ ልጆች እንዲወለዱ በማድረግ ጤነኛ ቤተሰብ ለመመስረት የወደፊት ሕይወትን በዕቅድ ለመምራት የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ለመጠቀም የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክንያት ለሚከሰቱ ተጓዳኝ በሽታዎች ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ ለማድረግ መግቢያ በር ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በክልሉ *279* የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ በፀረ ኤድስ ዘመቻ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ቅስቀሳ እየተደረገ ከመሆኑም በላይ በክልሉ የማህበረሰብ ውይይት እየተካሄደ በመሆኑና ከፍተኛ የሆነ የመመርመር ፍላጎት በመፈጠሩ ከመደበኛ የአገልግሎት መስጫዎች በተጨማሪ በተንቀሳቃሽ ጣቢያዎችም አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የክልሉ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ከአጋር ድርጅቶችና ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ሲያካሄድ በነበረው የዘመቻ ሥራ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎቱ በነፃ /ያለ ክፍያ/ መካሄዱም በተጠቃሚው ህብረተሰብ በኩል ከፍተኛ ፍላጎት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ በሁሉም ዞኖች ለ1,789,165 ሰዎች የኤች.አይ.ቪ. የምክርና ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ1,645,833 ሰዎች አገልግሎቱ ተሰጥቷል፡፡ ይኼም ከዕቅዱ የ91.9% አፈፃፀም አለው፡፡ በዚህ ሪፖርት መሠረት ከተመረመሩት 978,052 ወንዶች ውስጥ 27,769 *(2.8%)* እንዲሁም ከተመረመሩት 664,878 ሴቶች መካከል 28,159 ***(4.23%)*** የሚሆኑት ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ተገኝቶባቸዋል፡፡ ከሪፖርቱ እንደምንገነዘበው ከተመረመሩት ውስጥ በቁጥር ወንዶቹ የሚበልጡ ቢሆንም ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የተገኘ ባቸውን ስንመለከት ግን የሴቶቹ ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በመከላከሉ በድጋፍ አሰጣጡ እንዲሁም በህክምናው በኩል ለሴቶች የተለየ ትኩረት የሚያስፈልግ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

የምክርና የደም ምርመራው መንግስታዊና መነግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እየተከናወነ ሲሆን በጃፓይጎ ኢትዮጵያ የባለሙያዎች አቅም ግንባታ፣የምክርና የደም ምርመራ ሞዴል ጣቢያ በማቋቋም፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት የልምድ ልውውጥና የመሳሰሉት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በማኔጅምንት ሳይንስ ፎር ሄልዝ በኩልም የሪፈራል ሲስተሙን ለማጠናከርና የአገልግሎት ጥራቱን ለማስጠበቅ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በክልሉ የኤች አይ ቪ. የደም ምርመራ በህ/ሰቡ እየተለመደ መሆኑን፣ ህብረተሰቡም ከኤች.አይ.ቪ. ተጋላጭነት ራሱን የመጠበቅ ልምዱ መሻሻሉን እንዲሁም እየተካሄዱ ያሉት የመከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ውጤታማ እየሆኑ እንደመጡ ያመለክታል፡፡

# የ2001 የምክርና የደም ምርመራ ዕቅድ አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ዞን | ዓመታዊ ዕቅድ | VCT | | | | | | PIHCT | | | | | | ለህክምና ክትትል ሪፈር የተደረጉ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ያደረጉ | | | ቫይረሱ የተገኘባቸው | | | የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ያደረጉ | | | ቫይረሱ የተገኘባቸው | | | | | |
| | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ደ/ወሎ | 280000 | 195901 | 146055 | 341956 | 3486 | 5207 | 8693 | 12385 | 11574 | 23959 | 843 | 1124 | 1867 | 1012 | 1451 | 2463 |
| 2 | ሰ/ሸዋ | 231775 | 145706 | 94565 | 240271 | 1892 | 2644 | 4536 | 2515 | 2850 | 5365 | 241 | 328 | 569 | 175 | 280 | 455 |
| 3 | ምስ/ጎጃም | 245758 | 137045 | 62276 | 199321 | 1705 | 1846 | 3551 | 12570 | 6490 | 19060 | 1248 | 1062 | 2320 | 1248 | 1062 | 2310 |
| 4 | አዊ | 98405 | 62199 | 50177 | 112376 | 556 | 938 | 1494 | 1531 | 3739 | 5470 | 180 | 279 | 459 | 664 | 1027 | 1691 |
| 5 | ምዕ/ጎጃም | 174500 | 59137 | 31710 | 93649 | 679 | 1046 | 1725 | 1842 | 2146 | 3988 | 115 | 184 | 299 | ***69*** | ***115*** | ***184*** |
| 6 | ሰ/ጎንደር | 316500 | 74956 | 59029 | 133986 | 1797 | 2364 | 4161 | 3968 | 4649 | 8617 | 622 | 787 | 1410 | | | |
| 7 | ደ/ጎንደር | 145839 | 104586 | 64055 | 168641 | 8847 | 3528 | 12375 | 5235 | 6991 | 12226 | 251 | 399 | 650 | 121 | 230 | 351 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 96935 | 50872 | 39207 | 90079 | 2006 | 2496 | 4502 | 1971 | 2103 | 4074 | 271 | 393 | 634 | ***977*** | ***1270*** | ***2247*** |
| 9 | ዋግ ኽምራ | 98403 | 21218 | 15298 | 36416 | 232 | 253 | 485 | 930 | 1201 | 2131 | 84 | 113 | 197 | 26 | 32 | 58 |
| 10 | ኦሮሚያ | 76390 | 32623 | 27501 | 60124 | 255 | 391 | 646 | 1537 | 1680 | 3217 | 98 | 133 | 231 | 234 | 337 | 571 |
| 11 | ባህር ዳር | 76964 | 31204 | 29893 | 61097 | 2013 | 2475 | 4496 | 563 | 1689 | 2252 | 96 | 169 | 265 | 950 | 1355 | 2305 |
| | ድምር | ***1841469*** | ***915447*** | ***619766*** | ***1537916*** | ***23468*** | ***23188*** | ***46664*** | ***45047*** | ***45112*** | ***90359*** | ***4049*** | ***4971*** | ***8901*** | ***5476*** | ***7159*** | ***12635*** |

**ማሳሰቢያ፡ የዓመቱ ዕቅድ የጨመረበት ምክንያት ዞኖችና ወረዳዎች በማሻሻላቸው ምክንያት ነው፡፡**

## 1.1.4 ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል

የኤች.አይ.ቪን ሥርጭት ለመግታት ከፍተኛ ትኩረት ከተሠጣቸው ተግባራት መካከል አንዱ ከእናት ወደ ልጅ ቫይረሱ እንዳይተላለፍ መከላከል ነው፡፡ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የተገኘባቸው ነፍሰጡር እናቶች ኤች.አይ.ቪ. ወደ ህፃኑ እንዳይተላለፍ የሚያስችለውን ሕክምና እንዲያገኙ ግንዛቤ የመስጠትም ሆነ የአገልግሎቱ አትርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜም እየተስፋፋ ይገኛል፡፡

በበጀት ዓመቱ ኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ በ213 የጤና ድርጅቶች አገልግሎቱን የማቅረብ ስራ እየተሰራ ሲሆን ለ 144,633 እናቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 98,538 እናቶች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ክንውኑም የዕቅዱን 68.1% ሲሆን የዕቅድ አፈፃፀም ዝቅተኛ ቢሆንም ከአለፈው ዓመት ተማሳሳይ ወቅት ክንውን ጋር ሲነፃፀር በ 52,304 የአፈፃፀም መሻሻል የታየ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የኤች.አይ.ቪ. የደም ምርመራ ካደረጉት ነፍሰጡር እናቶች 3% ወይም 2,954 ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የተገኘ ሲሆን 1,726 እናቶችና 1,104 ህፃናት ኤች.አይ.ቪ. ወደ ህፃናት እንዳይተላለፍ የሚረዳ መድሀኒት አገልግሎት እንዲጠቀሙ ተደርገዋል፡፡

በተጨማሪ በተለያዩ ቦታዎች ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳተላለፍ የእናቶች ለእናቶች ድጋፍ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

# ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል እቅድ አፈጻጸም

| ተቁ | ዞን /ወረዳ | መለኪያ | አመታዊ ዕቅድ | የ2001 ክንውን | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የምክር አገልግሎት ያገኙ | ምርመራ ያደረጉ | ቫይረሱ የተገኘ ባቸው | NVP የወሰዱ እናቶች | NVP የወሰዱ ህፃናት | Partner Tested | |
| | | | | | | | | | የተመረ መሩ | ቫይረሱ የተገኘ ባቸው |
| 1 | ደ/ወሎ | ቁጥር | 89,000 | 23837 | 20583 | 642 | 497 | 223 | 2504 | **100** |
| 2 | ሰ/ሸዋ | " | 24,090 | 10021 | 9475 | 224 | 89 | 61 | **1822** | **26** |
| 3 | ምስ/ጎጃም | " | 33,600 | 14157 | 12112 | 224 | 216 | 134 | 2771 | **15** |
| 4 | አዊ | " | 13,699 | 9536 | 8685 | 287 | 100 | 102 | 2365 | **21** |
| 5 | ምዕ/ጎጃም | " | 25185 | 13353 | 11013 | 403 | 120 | 72 | 3128 | **12** |
| 6 | ሰ/ጎንደር | " | 10,000 | 20726 | 14411 | 472 | 304 | 220 | 1714 | |
| 7 | ደ/ጎንደር | " | 25771 | 10171 | 8438 | 200 | 139 | 87 | 2009 | |
| 8 | ሰ/ወሎ | " | 24440 | 6736 | 5229 | 242 | 145 | 124 | 870 | **72** |
| 9 | ዋግ ኸምራ | " | 7,224 | 1995 | 1355 | 27 | 15 | 2 | 8 | |
| 10 | ኦሮሚያ | " | 15,217 | 4696 | 4464 | 77 | 39 | 38 | 97 | **5** |
| 11 | ባህር ዳር | " | 7,224 | 2834 | 2773 | 156 | 62 | 41 | 270 | **1** |
| | ድምር | | *275,450* | *118062* | *98538* | *2954* | *1726* | *1104* | *17558* | *252* |

### 1.1.5 የኮንዶም ትውውቅና ሥርጭት

ጥንቃቄ የጎደለው የግብረስጋ ግንኙነት ዋና የኤች አይ ቪ መተላለፊያ መንገድ ከመሆኑ አንፃር ኮንዶምን በአግባቡና ሁልጊዜ መጠቀም በተለይም ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ማቅረብ አንዱ ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው፡፡ ዲኬቲ ኢትዮጵያና የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ኮንዶምን በማስተዋወቅና በማሠራጨት በዋናነት የሚሰሩ ሲሆኑ በሌሎች አካላትም ማለትም በቤተሰብ መምሪያ፣ በአልማ፣ በፀረ ኤድስ ክበባት፣ በግል የጤና ድርጅቶች እንዲሁም በሱቆችና በመድሐኒት ቤቶች ስርጭቱ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በበጀት ዓመቱ ጤና ጥበቃን ጨምሮ በተለያዩ አካላት 14986259 የወንድና 13741 የሴት ኮንዶሞችን ለማሠራጨት ታቅዶ በድምሩ 17699811 ወይም 118% የወንድ ኮንዶም ተሠራጭቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 2913600 በጤና ጥበቃና በሌሎች አካላት ፤ 10086211 በዲኬቲ ኢትዮጵያ ተሰራጭቷል፡፡ በተጨማሪም ከ I-TECH ኢትዮጵያ በተደረገ ግዢ ድጋፍ 1700000 ኮንዶሞች እንዲሁም ከፖፑሌሽን ሰርቪስ ኢንተርናሽናል 3 ሚሊዮን ኮንዶሞች በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴ/ጽ/ቤት በኩል በየደረጃው ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ ከዕቅድ አንፃር አፈፃፀሙ የሚያሳየው የክልሉ ህብረተሰብ የኮንዶም ተጠቃሚነቱና ስለኮንዶም ያለው ግንዛቤ መጨመርና ከኤች.አይ.ቪ ተጋላጭነት ራሱን የመጠበቅ በጐ አዝማሚያ እንዳለው ነው፡፡

### 1.1.6 የአባላዘር በሽታዎችን መከላከልና ማከም

የአባላዘር በሽታዎች የኤች አይ ቪ/ኤድስን ስርጭት ከሚያባብሱት ከዋና ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱ ሲሆን በአባለዘር በሽታዎች የተያዙ ሠዎች ለኤች.አይ.ቪ ያላቸው ተጋላጭነት ከጤነኛ ሰዎች ጋር ሲነፃፀር የበለጠ በመሆኑ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግና የተጋለጡትን ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ለ24,029 ሰዎች የአባላዘር በሽታ ሕክምና አገልግሎት ተሰጧል፡፡ ክንውኑም የዕቅዱ 31.6% ሲሆን ለመቀነሱ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት

1. ጥንቃቄ የጐደለው የግብረስጋ ግንኙነት ከማድረግ መቆጠብ፣
2. ኮንዶም በአግባቡ መጠቀም፣

3. ቶሎ ወደ ጤና ድርጅት ሂዶ መታከም መቻሉና ወደ ሌላው እንዳይተላለፍ መቻሉ፣

4. በፋርማሲ ሂዶ በቀጥታ በግል መድሃኒት በመጠቀም ሪፖርት አለመደረጉ፣

5. በጤና ድርጅቶች ለሪፖርቱ ያለው ትኩረት አናሳ መሆንና ከሪፖርት በታች መደረጉ፣

6. የአባላዘር በሽታ ህክምና መድኃኒት በጤና ድርጅቶች አለመኖር ታካሚዎች አለመሄዳቸው ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

በ2001 የበጀት ዓመት የአባላዘር በሽታ ሕክምና የተሰጣቸው ታካሚዎች ብዛት በዞን

| ተቁ | ዞን/ወረዳ | መለኪያ | አመታዊ ዕቅድ | ክንውን | | | ንፅፅር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | ደቡብ ወሎ | ቁጥር | 9,000 | 4698 | 4464 | 9162 | 101.8 |
| 2 | ሰ/ሸዋ | ቁጥር | 8,670 | 774 | 751 | 1525 | 17.5 |
| 3 | ምስራቅ ጎጃም | ቁጥር | 14,186 | 1485 | 1053 | 2538 | 17.9 |
| 4 | አዊ | ቁጥር | 1,476 | 472 | 375 | 725 | 49.1 |
| 5 | ምዕራብ ጎጃም | ቁጥር | 4,248 | 631 | 779 | 1410 | 33.2 |
| 6 | ሰ/ጎንደር | ቁጥር | 12,000 | 1323 | 1348 | 2671 | 22.2 |
| 7 | ደቡብ ጎንደር | ቁጥር | 9,161 | 675 | 744 | 1419 | 15.5 |
| 8 | ሰ/ወሎ | ቁጥር | 3,734 | 1070 | 893 | 1963 | 52.5 |
| 9 | ዋግ ኽምራ | ቁጥር | 8,319 | 366 | 381 | 889 | 10.7 |
| 10 | ኦሮሚያ | ቁጥር | 4,100 | 709 | 565 | 1214 | 29 |
| 11 | ባህር ዳር ከተማ | ቁጥር | 1,000 | 197 | 316 | 513 | 51.3 |
| | ድምር | | *75,894* | 12400 | 10925 | 24029 | 31.6 |

## *1.1.7 የማህበረሰብ ውይይት*

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ረገድ ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተከናወኑ ከሚገኙ ተግባራት አንዱ የማህበረሰብ ውይይት ነው፡፡ የማህበረስብ ውይይት በአለፉት ጥቂት አመታት ተጨባጭ ለውጥ በማምጣት አመርቂ ውጤት እንዲመዘገብ አስችሏል፡፡

የማህበረሰብ ውይይት በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ በቀጥታም ሆነ በተዛዋዋሪ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ላይ በመወያየት ችግሩን በመለየት አካባቢያዊ መፍትሔ በማስቀመጥ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በድጋፍና እንክብከቤ በአድልዎና መገለል ወዘተ ዙሪያ ጥልቅና ተከታታይ የሆነ ውይይት በማካሄድና ልዩ ልዩ ዉሳኔዎችን በማሳለፍ የህብረተሰቡን አቅም እያጐለበተ ይገኛል፡፡

የማህበረሰብ ውይይት ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከል በመቆጣጠር ድጋፍና እንክብካቤ እንቅስቃሴ እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ሲሆን ለአብነትም:-

- ከዚህ በፊት ለኤች አይ ቪ መስፋፋት ምክንያት የነበሩ በርካታ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲቀንሱ አድርጓል፣
- ህብረተሰቡ በድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት ጉልህ የሆነ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል፣
- ህብረተሰቡን ያሳተፈ የፀረ ኤችአይቪ/ኤድስ ንቅናቂ እንዲፈጠር አድርጓል ፣
- ህብረተሰቡ እያገኘ ባለው ግንዛቤ የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ከእናት ወደ ልጅ የቫይረሱን መተላለፍ በመከላከል እንዲሁም የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚነቱ እንዲጨምር አስተዋፅኦ አድርጓል።
- አድልዎና መገለል በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አድርጓል።ከዚህ በተጨማሪም የማህበረሰብ ውይይት ህብረተሰቡ ከጠባቂነት መንፈስ ተላቆ በልማት ስራ እንዲሳተፍ፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲሳተፉ አይነተኛ መፍትሄ እየሆነ ይገኛል።

የማህበረሰብ ውይይት የሚካሄድባቸው ቀበሌዎች ብዛት 3426 ሲሆኑ የጣቢያዎች ቁጥር ደግሞ 3877 የማህበረሰብና 377 የትምህርት ቤት በድምሩ 4250 ደርሷል። በአጠቃላይ 324224 ያህል ተሳታፊዎች ውይይቱን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። ቀጥታ ባልሆነ (በተዘዋዋሪ) የውይይት ተሳታፊዎቹ በቤተሰብና በአካባቢ አምስት ሰዎችን በመረጃ ልውውጥ ቢደርሱ 1,621,120 ያህል ህዝብ ተጠቃሚ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ከውይይቱ ተሳታፊዎች *182282 (56.2%)* ያህሉ ወንዶች ሲሆኑ *141942 (43.8%)* ያህሉ ደግሞ ሴቶች ናቸው።

## በበጀት ዓመቱ በማ/ሰብ ዉይይት  አስልጣኞችና አመቻቶች ብዛት በዞን ደረጃ

| ዞን | የአሰልጣኞች ብዛት | | | የውይይት የአመቻቾች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| ባ/ዳር | 6 | 2 | 8 | 26 | 48 | 74 |
| ምዕ/ጉጃም | 11 | 2 | 13 | 165 | 611 | 776 |
| አዊ | 10 | 1 | 11 | 43 | 375 | 418 |
| ምስ/ጉጃም | 28 | 3 | 31 | 602 | 771 | 1369 |
| ሰ/ሸዋ | 32 | 6 | 38 | 453 | 733 | 1186 |
| ኦሮሚያ ብ/ሰብ | 11 | 4 | 15 | 93 | 141 | 234 |
| ደ/ወሎ | 52 | 1 | 53 | 97 | 561 | 658 |
| ሰ/ወሎ | 10 | 61 | 71 | 289 | 538 | 827 |
| ዋግኸምራ | 6 | 0 | 6 | 79 | 186 | 265 |
| ደ/ጎንደር | 12 | 1 | 13 | 186 | 536 | 722 |
| ሰ/ጎንደር | 25 | 6 | 31 | 265 | 641 | 906 |
| ድምር | 203 | 87 | 290 | 2298 | 5141 | 7435 |

## የማ/ሰብ ዉይይት ተሳታፊዎች ብዛት በዞን በነባርና በአዲስ የውይይት ጣቢያዎች

| ዞን | የማ/ሰብ ውይይት የሚካሄድባቸው ቀበሌዎች | ጠቅላላ የጣቢያዎች ብዛት | ነባር ጣቢያዎች ብዛት | ነባር ጣቢያዎች የተሳታፊዎች | | | አዲስ ጣቢያዎች ብዛት | አዲስ ጣቢያዎች የተሳታፊዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወ | ሴ | ድ | | ወ | ሴ | ድ |
| ባ/ዳር | 21 | 26 | 26 | 999 | 1031 | 2030 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ምዕ/ጉጃም | 360 | 362 | 216 | 7845 | 6541 | 14386 | 156 | 6167 | 4323 | 10490 |
| አዊ | 193 | 202 | 202 | 10479 | 4735 | 15214 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ምስ/ጉጃም | 426 | 501 | 217 | 14171 | 10998 | 25232 | 213 | 16563 | 9997 | 26560 |
| ሰ/ሸዋ | 424 | 452 | 405 | 25202 | 15398 | 40198 | 47 | 5226 | 3957 | 8466 |
| ኦሮሞ ብ/ሰብ | 112 | 114 | 114 | 3818 | 2560 | 6378 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ደ/ወሎ | 517 | 566 | 172 | 3870 | 3870 | 7740 | 388 | 8730 | 8730 | 17460 |
| ሰ/ወሎ | 309 | 466 | 374 | 14892 | 13028 | 27920 | 68 | 5175 | 4835 | 10010 |
| ዋግኸምራ | 125 | 168 | 141 | 5783 | 4437 | 10230 | 27 | 1090 | 878 | 1968 |
| ደ/ጎንደር | 335 | 471 | 172 | 7505 | 5579 | 13084 | 299 | 10401 | 6054 | 19565 |
| ሰ/ጎንደር | 571 | 549 | 410 | 15196 | 11099 | 26295 | 89 | 3238 | 2700 | 5938 |
| ድምር | 3426 | 3877 | 2449 | 109760 | 79276 | 188707 | 1287 | 56590 | 41474 | 100457 |

## የት/ት ቤት የማ/ሰብ ዉይይት ተሳታፊዎች ብዛት በዞን በነባርና በአዲስ የውይይት ጣቢያዎች

| ዞን | የአሰልጣኝ ብዛት | | | የውይይት አመቻቾች ብዛት | | | ስራ ያልጀመሩ አመቻቾች ብዛት | | | የት/ት ቤቶች ብዛት | የተሳታፊዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | | ወ | ሴ | ድ |
| ምዕ/ጉጃም | 8 | 2 | 10 | 77 | 55 | 132 | 10 | 8 | 18 | 66 | 2390 | 2255 | 4645 |
| አዊ | 4 | 1 | 5 | 90 | 32 | 122 | | | | 48 | 2429 | 1872 | 4299 |
| ምስ/ጉጃም | | | 62 | | | 168 | | | | | | | |
| ሰ/ሸዋ | | | | 51 | 25 | 86 | | | | 79 | 3568 | 3062 | 6630 |
| ኦሮሞ ብ/ሰብ | 6 | 1 | 7 | 30 | 20 | 50 | 3 | 1 | 4 | 15 | 630 | 509 | 1139 |
| ደ/ጎንደር | 9 | 3 | 12 | 125 | 80 | 205 | 29 | 16 | 45 | 93 | 3354 | 8335 | 11689 |
| ሰ/ጎንደር | | | | | | 354 | | | | | | | |
| ዋግኽምራ | | | | | | 45 | | | | | | | |
| ሰ/ወሎ | 4 | 1 | 5 | 104 | 38 | 142 | | | | 72 | 3561 | 3097 | 6658 |
| ድምር | 31 | 8 | 101 | 477 | 250 | 1304 | 42 | 25 | 67 | 373 | 15932 | 19130 | 35060 |

ማሳሰቢያ፡ሌሎች ዞኖች የትምህርት ቤት የማህበረሰብ ውይይት ሪፖርት አላኩም፡፡

## የማህበረሰብ አቀፍ ኤድስ ፕሮግራም

ይህ ፕሮግራም በአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ሲደገፍ የቆየ ከማህበረሰብ ውይይት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ህብረተሰቡን የሚያሳትፍ ፕሮግራም ሲሆን በክልሉ አራት ወረዳዎች (እስቴ፣ አቸፈር፣ ዓንጓ እንዲሁም ወንበርማ) በ40 ቀበሌዎች በተጠናከረ ሁኔታ የተካሄደ ሲሆን፣ በግሎባል ፈንድ ድጋፉ ተጨማሪ 1,000 ቀበሌዎች እንዲታቀፉ ተደርጎ በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ 6,240 የበጎ ፈቃድ ፀረ ኤድስ መልዕክተኞች የአሰልጣኞች ስልጠና ወስደው ወደ ስራ በመሰማራት ተፈፃሚ እየሆነ ይገኛል፡፡ በተጨማሪ 11660 በጎ ፈቃደኞች ስልጠና ወስደው ለ233200 ቤተሰብ መድረስ ተችሏል፡፡ ህብረተሰቡ እራሱን ከወረርሽኙ በመከላከል ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ ለሌሎች አከባቢዎች አርዓያ ሊሆን የሚችል የባለቤትነትና ሃላፊነት የሚፈጥር ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ዋና ዋና ተግባራትም ስልጠናዎች፣ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አሳታፊ የሆነ የምክክር ፕሮግራምና የተሻሉ ስራዎች የልምድ ልውውጥ የሚከሄድበትና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

### በስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከል

የመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ልዩ ልዩ ተቋማት በስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪን በመከላከል እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሠረት አበረታች ጅምሮች እየታዩ ነው፡፡ በሲቪል ሰርቪስና በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ የተዘጋጀውን የስራ ቦታዎች መመሪያ በማስተዋወቅና አፈፃፀም በመከታተል፣ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ያለባቸውን ሠራተኞች መብት ከማስጠበቅ አኳያ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ለአብነትም በክልል ደረጃ 11 ሠራተኞች ከሌሊት ወደ ቀን፣38 ሠራተኞች ምደባ እንዲያገኙ በማድረግ፣16 ከስራ የተሰናበቱ ወደ ስራ እንዲመለሱ በማድረግ፣20 ሠራተኞች በሚመጥናቸው ስራ እንዲመደቡ፣65 ሠራተኞች ወደ ቤተሰቦቻቸው በዝውውር እንዲቀላቀሉ የማድረግ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

### *1.1.8 ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተከናወኑ ተግባራት*

ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ለኤች አይ ቪ. የተጋለጠ ቢሆንም ነገር ግን በስራ ባህሪያቸዉ በፆታና በዕድሜ የበለጠ ለኤች.አይ.ቪ. የተጋለጡ አካላት ላይ ትኩረት በማድረግ በአነስተኛ ወጭ ጊዜና የሠዉ ሃይል በፍጥነት የተሻለ ውጤት ማምጣት የሚቻል በመሆኑ የተለየ ጥረት እንዲደረግ ይጠበቃል፡፡ ከእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎችም ወጣቶች፣ ሴቶች፣ መለዮ ለባሹ፣ ተንቀሳቃሽ ሠራተኞች፣ሹፌሮች እና መምህራን ይገኙበታል፡፡ ከላይ በተገለፁት ተግባራት ተጠቃሎ የቀረበ

ቢሆንም ለነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች የተደረገውን ጥረት ለማሳየትና ወደፊትም አጠናክሮ ለመቀጠል እንደሚከተለው ተገልፆአል፡፡

- ወጣቱን ትኩረት ያደረጉ በፀረ ኤድስ ክበባት አማካኝነት በድራማ በስነ ጽሑፍ በሙዚቃ በመነባነብና በመሳሰሉት በመከላከሉ ዙሪያ በክልሉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡
- በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ላሉ የፀረ ኤድስ ክበባትንና የመረጃ ማዕከላትን፣ ሚኒሚዲያዎችን በማkkምና በማጠናከር ወጣቱን ከኤች አይ ቪ እንዲከላከል እየተደረገ ነው፡፡ የአቻ ለአቻ ውይይቶችም እየተካሄዱ ናቸው፡፡ ለአብነትም በባህር ዳር ከተማ 1086 ወጣቶች የሚሳተፉበት 22 መድረኮች ይገኛሉ፡፡በሴቶች ማህበር በኩል ከ18 ት/ት ቤቶች ለተውጣጡ 47200 ሴት ተማሪዎች ስለ ስነተዋልዶና ኤች.አይ.ቪ እንዲሁም ስለፆታዊ ጥቃት ትምህርት ተሰጥቷል፡፡
- ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል እንዲጠቀም የሚበረታታ ቢሆንም በተለይም ወጣቱና መለዮ ለባሹ የህብረተሰብ ክፍል ከዕድሜውና ከስራ ባህርይው አንፃር ኮንዶም እንዲጠቀም ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም የኮንዶም አቅርቦት በስፋት እየተካሄደ ይገኛል፡፡ይህም ወጣቱንና የመለዮ ለባሹን ከቫይረሱ ከመጠበቅ አንፃር ትልቅ ፋይዳ አለዉ፡፡
- የኤች.አይ.ቪ ስርጭት ከፍተኛ ደረጃ በደረሰባቸው የክልሉ የተመረጡ አካባቢዎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ትኩረት ያደረገ ጥናት ተጠናቋል፡፡ ጥናቱን መነሻ በማድረግም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን በዕቅድ ዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡
- በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ በርካታ የመከላከልና ድጋፍ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን በተለይም በሴተኛ አዳሪዎች ላይ ከተሰሩ ስራዎች ሁለገብ የመከላከል ስልጠና፣ የአቻ ለአቻ ትምህርት፣ የንግድ ክህሎት ስልጠናና የመነሻ ካፒታል መስጠት ይገኙበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኤች.አይ.ቪ ላለባቸው ሴቶች በገቢ ማስገኛ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡በተለያዩ ዞኖች በሆቴል ተቀጥረው ለሚሰሩ፣የስልጠናና የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ለረዳትና ሾፌሮች፣ ተማሪዎችና መምህራን፣ ለፖሊሶችና ለሌሎች የህይወት ክህሎት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በክልሉ ከፍተኛ የሆነ የባህርይ ለውጥ እያመጣ ያለው የማህበረሰብ ውይይት ላይም ሴቶች ቢያንስ *50* በመቶ እንዲሆኑ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

♦ በክልሉ ውስጥ በሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች(በመንገድ ስራ፣በመስኖ ልማት)፣በሰፈራ አካባቢ፣በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካባቢ የሚገኘውን ህብረተሰብና የፕሮጀክት ሠራተኞች ከኤች.አይ.ቪ ለመጠበቅ ትኩረት በመስጠት በርካት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

በአጠቃላይ በመከላከሉ ዘርፍ ከላይ በተዘረዘሩት የትኩረት መስኮች በልዩ ልዩ አካላት በርካታ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን በተቋም ደረጃ በስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከል እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ በልዩ ልዩ መንገዶች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ እነዚህ ተግባራትም ከለጋሽ ድርጅቶችም ሆነ ከአካባቢው በተገኘ ሃብት ተከናውኗል፡፡

## *2. ድጋፍና ክብካቤ*

ድጋፍና ክብካቤ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ይሰጠዋል፡፡ ስለሆነም በክልላችን ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝና ለኤድስ ህሙማን እንዲሁም ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች በርካታ ፈፃሚ አካላትና ማህበራት በኩል ድጋፍና ክብካቤ እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል፡፡

### 2.1. ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝባቸውና ለኤድስ ህሙማን ድጋፍና የማህበራት እንቅስቃሴ

በ2001 በጀት አመት በድምሩ ለ141926 ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝና ኤድስ ህሙማን ድጋፍና ክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ ለ66890 ሰዎች በተለያዩ የድጋፍ አይነቶቸ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ክንውኑም 47.1% ሲሆን ፤21 ሰዎች ከክልል ቢሮዎች በቃሚነት በየወሩ የሚደገፉ ይገኙበታል፡፡ የተሰጡ የድጋፍ አይነቶችና የተጠቃሚዎች ብዛት እንደሚከተው ይሆናል፡፡

- ✓ የስነ ልቦና የምክር አገልግሎት ማህበራዊ ድጋፍ------29862
- ✓ የምግብ ድጋፍ-----------------------------------18968
- ✓ የመጠለያ ድጋፍ-----------------------------------3789
- ✓ የገቢ ማስገኛ ስልጠና ድጋፍ ---------------------6360
- ✓ ለገቢ ማስገኛ ስራ የበጀት ድጋፍ ------------7911 በጥቅሉ 66890 ሰዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የተገኘባቸው ወገኖች  የድጋፍና እንክብከቤ አገልግሎት እቅድ አፈጻጸም

| ድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት የስራ ዝርዝር | መለኪያ | የአመት እቅድ | ክንውን | % |
|---|---|---|---|---|
| የስነ ልቦና የምክር አገልግሎት ማህበራዊ ድጋፍ | የተደገፉ | 47304 | 29862 | 63.1 |
| የምግብ ድጋፍ | የተደገፉ | 50741 | 18968 | 37.7 |
| የመጠለያ ድጋፍ | የተደገፉ | 20803 | 3789 | 18.2 |
| በገቢ ማሰገኛ ተግባራት ስልጠና ድጋፍ ማድረግ | የተደገፉ | 15851 | 6360 | 40 |
| ለገቢ ማስገኛ ተግባራት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ | የተደገፉ | 7227 | 7911 | 109.5 |
| ድምር | | **141926** | **66890** | **47.1** |

በክልሉ በአጠቃላይ 135 የሚሆኑ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ የተገኜባቸዉ ሰዎች ማህበራት ተደራጅተው አባሎቻቸው በተለያዩ የገቢ ማስገኛ የድጋፍና ክብካቤ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልም የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር እንዲሁም በሌሎች ተግባራት እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ያለባቸዉ ሰዎች ማህበራት አባላት የተሰማሩባቸዉ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ዉስጥ ዋና ዋናዎቹ፤

- ሰብል ምርት
- በእንስሳት እርባታና ማድለብ
- በሽቀጣሽቀጥ ንግድ
- ወፍጮ ቤት
- በሆቴል አገልግሎት
- በካፍቴሪያ አገልግሎት
- በጽህፈት መሳሪያዎች

  አገልግሎት ወዘተ

  ይገኙባቸዋል፡፡

በድጋፍና ክብካቤ በኩል የአለም ምግብ ፕሮግራም በ7 ከተሞች (ባ/ዳር፤በጎንደር፤ደሴ፤ደ/ብርሃን፤ ወልድያ፤ደ/ማርቆስና በኮምቦልቻ) በተለያዩ ፈጻሚ አካላት (በኦሳ፤መቅድም፤ተስፋ ጎህ፤ማህበረ ህይወት፤ሲቪኤም፤አናፒካን፤ቀይመስቀልና ቤተሰብ መምሪያ) በኩል እየተከናወነ ያለዉ የአልሚ ምግብ ድጋፍ በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ያለና የሚያበረታታ ወጤት እያስገኘ ያለ ተግባር ነዉ፡፡

### *2.2. ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች የሚደረግ ድጋፍ*

ወላጆቻቸውን በኤድስና በሌሎች ምክንያቶች የሚያጡ ተጋላጭ ልጆች ቁጥር ከሚደረገው የድጋፍና ክብካቤ ምላሽ በላይ በመሆኑ በርካታ ልጆች ለጎዳና ህይወትና ሌሎች ችግሮች እየተጋለጡ ይገኛሉ፡፡ የነዚህ ልጆች ችግሮች ዘላቄታዊ መፍትሄ የሚሹ ቢሆኑም በክልላችን የሚገኙ አጋር ድርጅቶችና ፈፃሚ አካላት ከተለያዩ ምንጮች በሚገኘውና በአካባቢው ሃብት የገንዘብ ድጋፍ ለጥቂቶቹ የመሠረታዊ ፍላጐትና የትምህርት ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በበጀት ዓመቱ *138981(38%)* ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ልጆች የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በየደረጃዉ በተደረገዉ ድጋፍ የተጠቃሚወች ብዛት በድጋፉ አይነት ሲታይ

- ✓ የስነ ልቦና የምክር አገልግሎት ማህበራዊ ድጋፍ ........*47275*
- ✓ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ........................................*51061*
- ✓ የምግብ ድጋፍ..........................................................*19243*
- ✓ የመጠለያ ድጋፍ.......................................................*1959*
- ✓ የገቢ ማስገኛ ስልጠና ድጋፍ .............................................7332
- ✓ ለገቢ ማስገኛ ስራ የበጀት ድጋፍ................................12111 ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ልጆች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ (ዕቅድ ክንውኑ በቀጣዩ ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡)

በተለያዩ ረጂና ፈጻሚ ድርጅቶች የተከናወኑ የመሠረታዊና የትምህርት ድጋፎች እንዲሁም የገቢ ማስገኛ ተግባራት ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ልጆች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉና ጤናማ ዜጐች እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ ከላይ በተገለጸው ድጋፍ 146 ወላጆቻቸዉን ያጡና ተጋላጭ ህጻናት በክልል ቢሮዎች፣763 በዞንና በወረዳ የሴክተር መ/ቤቶች ኤድስ ፈንድ አማካይነት በየወሩ 150.00–300.00 በአሳዳጊዎቻቸው በኩል እየተሰጠ

ትምህርታቸዉን በመቀጠል ላይ ሲሆኑ በተለይም የክልሉ ዉሃ ሃብት ልማት ቢሮ ለ9 ህጻናት በየወሩ 150.00 ብር እያደረገ ያለዉ ድጋፍ በዓርዓያነት የሚጠቀስ ነዉ፡፡

**ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች የተደረገዉ ድጋፍ እቅድ አፈጻጸም**

| ዝርዝር ተግባራት | መለኪያ | የአመት እቅድ | ክንውን | % |
|---|---|---|---|---|
| ድጋፍና ክብካቤ ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ህፃናት | የተደገፉ ህፃናት | | | |
| የስነ ልቦና የምክር አገልግሎትና ማህበራዊ ድጋፍ | የተደገፉ ህፃናት | **63840** | **47275** | **74** |
| የትምህርት ድጋፍ /የት/ቤት ክፍያ፣ የት/ቁሳቁስ/ የደንብ ልብስ/ | የተደገፉ ህፃናት | **171344** | **51061** | **30** |
| የምግብ ድጋፍ | የተደገፉ ህፃናት | **78357** | **19243** | **24.5** |
| የመጠለያ ድጋፍ | የተደገፉ ህፃናት | **43163** | **1959** | **4.5** |
| በገቢ ማሰገኛ ተግባራት ስልጠና መስጠት | የተደገፉ ህፃናት | **6007** | **7332** | **122** |
| ለገቢ ማስገኛ ተግባራት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ | የተደገፉ ህፃናት | **3586** | **12111** | **337.7** |
| ድምር | | 366297 | *138981* | 38 |

## *2.3. የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት አገልግሎት*

ክልላችን የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት በሚያስፈልጋቸው ሰዎች ብዛት ቀዳሚውን ስፍራ የያዘ በመሆኑ አገልግሎቱን በስፋት ማዳረስ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይሄን አገለግሎት ለማዳረስ የጣቢያዎችን ቁጥር መጨመር፣ የሰው ኃይል ማሰልጠንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን ማከናወን ከዚህም ጋር የመድሃኒቱ ተጠቃሚዎች ያለማቋረጥ እንዲጠቀሙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡

ከሁለት ዓመት ወዲህ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የመመርመር ፍላጐትና የፀረ-ኤች አይ ቪ መድሃኒት አገልግሎቶችን በመጠቀም ረገድ ከአመታት ጀምሮ ያልተመዘገቡ ውጤቶችን አስገኝተዋል፡፡ ባለፉት አመታት ለክልሉ ህብረተሰብ የተካሄዱት የግንዛቤ ማስጨበጫና የማህበረሰብ ውይይት ያስገኙት ለውጥ ትርጉም የሚሰጠው የነበር ቢሆንም በሶስቱ ዙር የሚሊኒየም ፀረ ኤድስ ዘመቻዎች የተካሄዱት የህዝብ ንቅናቄ ተግባራት ህብረተሰቡን የአገልግሎቶች ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

በዚህ የ2001 በጀት ዓመት አገልግሎቱ *በ17* ሆስፒታሎችና *በ87* ጤና ጣቢያዎች በድምሩ 104 የጤና ድርጅቶች አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በዓመቱ 89085 አዋቂዎችና 11656 ህጻናትን ቅድመ ጸረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት ለመስጠት ታቅዶ 88846 አዋቂዎችና 5559 ህጻናትን ለመስጠት ተችላል፡፡ይህም በቅደም ተከተል 99.7% እና 47.7% ነዉ፡፡በዚሁ የበጀት ዓመት 30000 አዋቂዎቸን እና ህጻናትን አዲስ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 23688 አዋቂዎችና ህጻናትን ተጠቃሚ ለማድረግ ተችላል፡፡ ከታቀደው 79% ተፈፃሚ ሆኗል፡፡

የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ዕድሜያቸው ከ14 ዓመት በታች የሆናቸው ልጆችና ህፃናት ቁጥር *6,167* እንደሚደርስ ቢገመታም የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት የህፃናትና ልጆች ህክምና አገልግሎት በሆስፒታል ተወስኖ በመቆየቱና ህብረተሰቡ ህፃናትና ልጆችን የማስመርመርና ፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ግንዛቤው የሚፈልገውን ያህል ባለመሆኑ ችግሩ እየጎላ መጥቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የህንፃናትና ልጆች የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ህክምና በአግባቡ ሪፖርት እንደማይደረግ መረዳት ተችሏል፡፡

# 3. የአቅም ግንባታ

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዘርፈብዙ ምላሽ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በየደረጃው ያሉ ፈፃሚና አስፈፃሚ አካሎችን አቅም ማጠናከር በበጀት ዓመቱ ትኩረት የተሰጠው ተግባሮች ነበሩ፡፡ በመሆኑም ለእነዚህ አካላት የተለያዩ ቁሳቁሶች ድጋፍ፣ የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተከናውነዋል፡፡

3.1 **መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ** - ጽ/ቤቱ ዉጤት ለማምጣት በሚያስችለው መልኩ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ያከናወነ ሲሆን ከክልሉ ጽ/ቤት እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ ሊያሰራ የሚችል የBPR ጥናት ተካሂዶል፡፡ ጥናቱም ፀድቆ በክልል ደረጃ የሰው ሀይል ምደባ ተካሂዶል፡፡ የሙከራ ትግበራ በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡

ዋና የስራ ሂደቶች

- በጋራ የማሳቀድና የመከታተል ዋና የስራ ሂደት
- የቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት
- የመረጃና የህዝብ ግንኙነት ዋና የስራ ሂደት
- የሃብት አሰባሰብና አስተዳደር ዋና የስራ ሂደት ናቸው

ደጋፊ የስራ ሂደቶች

- የግዥና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት
- የሰው ሀይል አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት
- የኦዲት አገልግሎት
- የ ICT አገልግሎት

በተጨማሪም በክልሉ የስራ አመራር ተkም ሁሉም የስራ ሂደት ባለቤቶች የ6 ቀናት ስልጠና በ BSC (ውጤት ተኮር) አተገባበር ላይ ሰልጥነዋል፡፡ 326 የጽ/ቤታችን ሰራተኞች ለ3 ቀናት BPR አተገባበር ስልጠና በወልድያና በባህር ዳር ተሰጥታል፡፡

ለሁሉም የፀደቁ የስራ ሂደቶች የጥናት ሰነዶችና የማስተግበሪያ መሳሪያዎች፣ የማስፈፀሚያ ዕቅድ እና የቡድን አባላት የመግባቢያ ሰነድ እና የመሳሰሉት ተሚልተዋል፡፡

3.2 በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ወርክሾፖችና አውደጥናቶች

- ለ239 የክልልና 150 የባህርዳር ከተማ ምክር ቤት ኣባላት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ.መቆ.ተግባር መደበኛ ስራ አድርገው ክትትል እንዲያደርጉና እንዲገመግሙ የ 1 ቀን ወርክሾፕ ተካሂዶል፡፡
- ለ154 የዞን፣ የወረዳና ከተማ አስተዳደር አፈ ጉባኤዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ.መቆ. ተግባር መደበኛና ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ስራ አድርገው ክትትል እንዲያደርጉና እንዲገመግሙ የ 1 ቀን ወርክሾፕ ተካሂዶል፡፡
- ከክልሉ ሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች ለተውጣጡ 1350 ሴቶችና 61 ወንዶች በድምሩ 1411 ሰዎች የ PMTCT አገልግሎት ህ/ሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን አስመልክቶ የ2 ቀን ወርክሾፕ ተካሂዶል፡፡
- በክልሉ የሚገኙ 137 ሁሉም ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች ማህበር ሊቀመንበሮች ጋር የጋራ የ1 ቀን የምክክር መድረክ ተካሂዶል፡፡
- 80 የሀይማኖት ተወካዮች፣ 80 የንግድ ማህበረሰብ ተወካዮች እንዲሁም 60 ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ተkሞች ለተውጣጡ ሰዎች የ 2 ቀን ወርክሾፕ ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት በማ/ሰቡ ሊደረግላቸው ስለሚገባ ድጋፍ ውይይት ተደርጓል፡፡
- በዩኒሴፍ አና ዩኤንኤፍፒኤ በጋራ የተዘጋጀውን የኖራድ ፕሮግራም በክልላችን ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም የሚመለከታቸው አጋር አካላት 60 ሰዎች ባሳተፈ መልኩ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፣ የትውውቅ ወርክሾፕ 100 የሚመለከታቸው በተገኙበት ተካሂዶል፤ ስራዉን ለመስራት የሚያስፈልግ የሰው ሀይል ተሟልቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡
- በሲዲሲ ድጋፍ በክልላችን ከፍተኛ ተጋላጭነት ባለባቸው አካባቢዎችና የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተጠናውን ጥናት መሰረት በማድረግ የሚመለከታቸውን አጋር አካለት ባሳተፈ መልኩ የዕቅድ ዓውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡
- ከሀይማኖት አባቶች ጋር ስለፀረ-ኤች.ኤ.ቪ. መድሀኒትና ጸበል እንዲሁም ፆም ያላቸው ቁርኝት አስመልክቶ የ2 ቀን ወርክሾፕ ተካሂዶል፡፡
- ክልል አቀፍ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከል ድጋፍና ክብካቤ እና የህክምና ስራዎች የተገመገመበት ኮንፍረስ 520 ሰዎች የተሳተፉበት ከሰኔ 15-17/2001 ዓ.ም ተካሄዷል፡፡

- 109 ሰዎችየተሳተፉበትየመንግስት ሴክተሮች፤የከፍተኛ ትምህርት ተቃማት፤የመያድ፤ የትብብር ፎረሞች አዉደ-ጥናት ተካሄዳል፡፡
- 453 በ 5 የጤና ኮሌጆች የሚገኙ መደበኛ ተማሪዎች የምክርና ምርመራ አገልግሎት ስልጠና ተሰጥታል፡፡

## 3.3 የጤና አገልግሎት መስጫ ተkማትን ማስፋፋት

| ተ. ቁ | ተግባራት | መለኪያ | በዚህ በጀት ዓመት በአዲስ ማስጀመር | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የዓመት ዕቅድ | ክንውን | ንፅፅር | በ2000 በጀት ዓመት ላይ የነበረ | አሁን የተደረሰ |
| 1 | kሚ የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ ጣቢያዎችን ማስፋፋት | ቁጥር | 79 | 145 | 183.5 | 205 | 350 |
| 2 | የ PIHCT ጣቢያቸን ማስፋፋት | ቁጥር | 124 | 88 | 70.96 | 205 | 293 |
| 3 | kሚ የPMTCT አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ማስፋፋት | ቁጥር | 72 | 45 | 62.5 | 168 | 213 |
| 4 | የፀረ ኤች አይ ቪ መድሀኒት ህክምና አገልግሎት /የህፃናትን ጨምሮ/ በመንግስት ተቋማት ማስፋፋት | ቁጥር | 73 | 27 | 36.9 | 77 | 104 |
| 5 | የፀረ ኤች አይ ቪ መድሀኒት ህክምና አገልግሎት /የህፃናትን ጨምሮ/ በግል ተቋማት ማስፋፋት | ቁጥር | 8 | 2 | 25 | | |
| 6 | የተንቀሳቃሽ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ ጣቢያ ማቋቋም | ቁጥር | 700 | 1087 | 155.3 | | 1087 |
| 7 | የኮንዶም ማሰራጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም | ቁጥር | 6213 | 1052 | 16.9 | | 1052 |

ማሳሰቢያ፡

- ☞ የፀረ- ኤች.አይ.ቪ. ህክምና የሚሰጥባቸው 17 ሆስፒታሎች 86 በMSH የሚደገፉ ጤና ጣቢዎችና 1 በMSF-Holland የሚደገፍ ጤና ጣቢያ ናቸው፡፡ 74 የHCT፣ 52 የ PHICT፣ 45 የ PMTCT፣ 27 የ ART፣ በድምሩ 198 የጤና አገልግሎት መስጫ ተkማት በአዲስ የጀመሩ ሲሆን 1052 የኮንዶም ማሰራጫ ጣቢያዎች ተkቁመዋል፡፡

በተጨማሪ በ1087 የ Mobile VCT እየተሰጠ ይገኛል፡፡

### 3.4 በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መረጃ የሚሰጡ ማዕከላትን ማkkምና ማጠናከር

| ተ.ቁ | ተግባራት | መለኪያ | የዓመት ዕቅድ | ክንውን | ንፅፅር | አስተያዮት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የኤድስ መረጃ ማዕከላትን ማቋቋም ከት/ቤት ውጭ | በቁጥር | 1414 | 232 | 17 | |
| 2 | የኤድስ መረጃ ማዕከላትን በት/ተቋማት ማቋቋም | በቁጥር | 39 | 80 | 216 | |
| 3 | የት/ቤት ሚኒ ሚዲ ማእከላት መመስረት | በቁጥር | - | 560 | | ከዕቅድ ውጭ የተከናወነ |
| 4 | የወጣቶች ዮዝ ፍሬንድሊ የኤድስ መረጃ ማእከል መመስረት | በቁጥር | 100 | 173 | 173 | |
| 5 | የትምህርት ተቋማት ፀረ-ኤድስ ክበባትን አቅም መገንባት/ማጠናከርና መመስረት | በቁጥር | 443 | 601 | 147 | |
| 6 | ከት/ቤት ውጭ ፀረ-ኤድስ ክበባትን መመስረት | በቁጥር | - | 69 | | ከዕቅድ ውጭ የተከናወነ |
| 7 | የወጣት ማዕከላትን ማkkምና በቁሳቁስ መደገፍ | ማዕከላት | 242 | 40 | 18 | |

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ መረጃ ለህብረተሰቡ እንዲደርስ የሚያግዙ በድምሩ 1755 ተkማት ተቋቁመዋል፡፡በዋነኛነትም የተkkሙት ማዕከላት በት/ቤት ውስጥና ከት/ቤት ውጭ ለሚገኙ ወጣቶች መረጃ የማግኘት ዕድል ይፈጥራሉ፡፡

### 3.5 ዋና ዋና ስልጠናዎች

| ተ.ቁ | ተግባራት | የዚህ በጀት ዓመት | | | | | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የዓመት ዕቅድ | | የ12 ወራት ክንውን | | | ንፅፅር | |
| | | | | ወ | ሴ | ድ | | |
| 1 | የማህበረሰብ ውይይት ለማካሄድ የተሰጡ ስልጠናዎች<br>• የማህበረሰብ ውይይት የአሰልጣኞች ስልጠና<br>• የማህበረሰብ ውይይት የአመቻቾች ስልጠና<br>• የትምህርት ማህበረሰብ ውይይት የአሰልጣኞች ስልጠና<br>• የትምህርት ማህበረሰብ ውይይት የአመቻቾች ስልጠና<br>• የማህበረሰብ ውይይት የአሰልጣኞች ማነቃቂያ ስልጠና<br>• የማህበረሰብ ውይይት የአመቻቾች ማነቃቂያ ስልጠና<br>• የት/ት ማህበረሰብ ውይይት የአሰልጣኞች ማነቃቂያ ስልጠና<br>• የት/ት ማህበረሰብ ውይይት የአሰልጣኞች ማነቃቂያ ስልጠና | 28900 | | | | 9647 | 33 | |
| 2 | የበጎ ፈቃደኛ ፀረ-ኤድስ መልዕክተኞች ስልጠና | 41112 | | | | 15713 | 38 | |
| 3 | የህይወት ክህሎት ስልጠና<br>• የአሰልጣኞች ስልጠና የወሰዱ<br>• የአመቻቾች ስልጠና የወሰዱ | 102436 | | 39247 | 29246 | 68493 | 66.9 | |
| 4 | የንግድ ክህሎት ስልጠና | 27215 | | | | 13990 | 51.4 | |
| 5 | ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ስልጠና | 3375 | | | | 2458 | 72. | |
| 6 | የአቻ ለአቻ ስልጠና | 3600 | | | | 4248 | 118 | |
| 7 | የቤት ለቤት ድጋፍና ክብካቤ ስልጠና | 1622 | | 414 | 782 | 1196 | 79 | |
| 8 | የወጣት ውይይት አመቻች ስልጠና | 200 | | 125 | 89 | 214 | 107 | |
| 9 | የባህሪ ለውጥ ስርጸት ስልተና | 3340 | | | | 1141 | 34 | |
| 10 | የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራም ማኔጅመንትና የፕሮጀክት ዝግጅት ስልጠና | 400 | | | | 994 | 248 | |
| 11 | የ VCT ስልጠና | 680 | | | | 86 | 12.6 | |
| 12 | የ PMTCT ስልጠና | 872 | | | | 385 | 44 | |
| 13 | የ ART ስልጠና | 512 | | | | 136 | 30 | |
| 14 | PHICT | | | 86 | 79 | 165 | | |
| 15 | TV/HIV | 757 | | 61 | 42 | 104 | 15 | |
| 16 | ሌሎች ስልጠናዎች (የፎካል ፐርሰን ውጤት ተኮር አስተቃቀድና መረጃ አያያዝ፣ የሂሳብ አያያዝ ስልጠና፣ ፖዘቲቭ አኖኖር፣ ሰብኣዊ መብት፣ አመራር፣ አድቮኬሲና ኔት ዎርኪንግ፣ የክበብ አመራር፣ ኮሚዩኒቲ ፕላኒንግ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ጎጂልማዳዊ ድርጊቶች፣ ስነተዋልዶ ስልጠናዎች) | | | | | 9390 | | |

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ ህክምና ለመስጠት እንዲሁም ድጋፍና ክብካቤ ለማድረግ የሚረዱ በርካታ ስልጠናዎችና የአቅም ግንባታ ተግባራት በተለያዩ አጋር አካላት እየተፈጸሙ ይገኛሉ፡፡

በድምሩ 128362 ሰልጣኞች በተለያዩና በየደረጃው ባሉ አጋር አካሎች የተሰጡ ስልጠናዎች ናቸው፡፡

የንግድ ክህሎት ስልጠና የተሰጣቸው መስራት የሚችሉ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት፣ ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ያለባቸው ወገኖችና ለተጋላጭ ወጣቶች( ሴተኛ አዳሪዎችን ጨምሮ) የተሰጠ ሲሆን ከስልጠና በ|ላም የመስሪያ ገንዘብ ድጋፍ፣ ቦታ እና ተገቢው ድጋፍና ክትትል ተደርጎላቸው ወደ ስራ ተሰማርተዋል፡፡

የህይወት ክህሎት ስልጠና የተሰጠው ከፍተኛ ተጋላጭነት ላላቸው የህ/ሰብ ክፍሎች ነው፡፡ በዋነኛነትም በስልጠናው የተሳተፉት ሴተኛ አዳሪዎች፣ ፖሊሶች፣ ተማሪወችና መምህራን፣ ወጣቶች እና ሹፌሮች ናቸው፡፡

ስልጠና በመስጠት በርካታ ተkማት የተሳተፉ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ

በየደረጃው ያሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ.መቆ.ማስ.ጽ/ቤትመያድ (CVM, MSH- care and support program, JHIPAIGO, World vision, care, ....) ሴክተር መ/ቤቶች ( ሴ/ጉ/ቢሮ፣ ጥ/አ/ን/ስ/ድ፣ ፍትህ ቢሮ፣ ሲ/ሰ/ኮ፣ ሠ/ማ/ጉ ቢሮ፣ ትምህርት ቢሮ፣ አስ/ፀጥታ . . .) ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ያለባቸው ወገኖች ማህበራት (የክልል ጥምረት፣ ፍኖት የሴቶች ጥምረት፣ ንጋት መንግስት ሰራተኞች ማህበር እና የመሳሰሉት) በየደረጃው የሚገኙ ሌሎች ፈፃሚዎች ናቸው፡፡

## 3.6 ጥናቶችንና ምርምሮችን መደገፍ

- ☞ በባህር ዳር ዩኒበርስቲ የቀረበዉ የ SMS ፕሮጀክት ተደግፋል፡፡
- ☞ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሰራተኞች ላይ እያደረሰ ያለዉ ጉዳት ጥናት ተደግፋል፡፡
- ☞ Infant feeding practice and factors affecting mothers choices of feeding among mothers enrolled in PMTCT program በሚል የቀረበ ጥናት ተደግፋል፡፡
- ☞ Prevalence of malnutrition and factors associated with in children attending HIV/AIDS care በሚል የቀረበ ጥናት ተደግፋል፡፡
- ☞ Mainstreaming at sectoral levels በሚል የቀረበ ጥናት ተደግፋል፡፡

- ☞ Water sanitation and hygien practice and associated factors among PLWHIV home based care services
- ☞ የክፍተት ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት አልቆ ወደስራ ተገብታል፡፡

## 3.7 በበጀት ዓመቱ ዋና ዋና የቁሳቁስ ድጋፍ

| ተ.ቁ | ተግባራት | የዓመት ዕቅድ | ክንውን | ንፅፅር | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በየደረጃው ላሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ.ቁጥ.ስራ/ማስ/ጽ/ቤቶች የቢሮ ቁሳቁስ ማሟላት<br>• ፎቶ ኮፒ<br>• ፕሪንተር<br>• ኤል.ሲ..ዲ<br>• ፋክስ<br>• ዳማ<br>• ቼዝ<br>• ቴብል ቴኒስ ከነ ራኬቱ<br>• መረብ ካስ ከነኔቱና ካሱ<br>• የእግርካስ<br>• ጠረጴዛ<br>• ወንበር | | 9<br>43<br>10<br>1<br>20<br>20<br>20<br>20<br>20<br>27<br>17 | | |
| 2 | የማህበረሰብ ሬዲዮ | 4200 | 4200 | 100 | |
| 3 | አዲስ ለተkkሙ የከተማ አስተዳደሮች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ.ቁጥ.ስራ.ማስ.ጽ/ቤቶችን በሰው ሀይልና በቁሳቁስ ማሞላት | 462 | 462 | 100 | |
| 4 | የቴስት ኪቶችና ሪኤጀንቶች አቅርቦት<br>• KHB<br>• STAT-PAK<br>• UNI-GOLD<br>• BLOOD LANCET<br>• EDTA capillary tube (100 pcs)<br>• EDTA capillary tube ( 200 pcs)<br>• Yellow tip (1000 pcs) | 36000<br>5400<br>540 | 27631<br>3166<br>625<br>8080<br>1845<br>3639<br>178 | | |
| 2 | የማህበራት፣ ፀረ-ኤድስ ክበባትና ኔትወርኮች አቀም ለመገንባት (ለወጣት ማዕከላትን ቁሳቁስ መደገፍ) | 242 | 40 | 18 | |

- በበጀት ዓመቱ ለጽ/ቤታችን ሁለት መኪናዎች በድጋፍ ከአለም ምግብ ፕሮግራምና ከወርልድ ቪዥን(አደጋ መከላከልና ዝግጁነት) ተገኝቷል፡፡
- አንድ ተሽከርካሪ ለሰሜን ጎንደር ዞን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ.ቁጥ.ስራ.ማስ.ጽ/ቤት ተሰጥቷል፡፡
- ለአማራ ክልል ዮዝ ኔትወርክ የ50000 ብር የቢሮ ቁሳቁስ ተሟልቶላቸዋል፡፡
- ለባህርዳር ከተማ ዮዝ ኔትወርክ የ7500 ብር የቢሮ ቁሳቁስ ተሟልቶላቸዋል፡፡

## 3.8 የማህበራት ድጋፍ

የክልሉ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች ጥምረት ቢሮ በሰው ሀይልና በቁሳቀስ እንዲጠናከር ተደርጓል፡፡

በየወረዳው የሚገኙ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ያለባቸው ወገኖች ማህበራት እንዲጠናከሩ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች፣ የቁሳቁስ እና የበጀት ድጋፍ ተደርጓል፡፡የክልሉ ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት ማህበር የቢሮ፣ የሰው ሀይል ቅጥር፣ የቢሮ ቁሳቁስ እና በጀት ድጋፍ ተደርጎለታል፡፡

## 3.9 በየደረጃው ያሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ማ/ጽ/ቤቶችን አቅም ማጠናከር

ከፌዴራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ.መቆ.ጽ/ቤት ጋር በመሆን ከፑልድ ፈንድ በተገኘ ድጋፍ በየደረጃው ያሉ የጽ/ቤቶቻችን ሰራተኞች ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን ሰልጣኞችና የስልጠና ተkሞች ተመርጠው በጀት በመጠበቅ ላይ እንገኛለን፡፡

በዚሁ ፕሮግራም 63 ሰራተኞች በርቀት ትምህርት - ዲፕሎማ ያላቸው ከሆነ ወደ ዲግሪ፣ ዲግሪ ያላቸው ከሆነ ደግሞ የማስተርስ ፕሮግራም እንዲማሩ ይደረጋል፡፡ የዚህ የሠው ሃይል ስልጠና ለጤናና ለማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ሠራተኞች የሚሰጥ ነው፡፡ 59 ሰራተኞች የአጭር ጊዜ ስልጠና - ለፋይናንስ ባለሙያዎች የፋይናንስ አስተዳደር ለፕሮግራም አስተባባሪወች ደግሞ የአመራርና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራም ማኔጅመንት የአጭር ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 3.10 ፎረሞችን አቅም ማጠናከር

| ተ.ቁ | ተግባራት | የዓመት ዕቅድ | ክንውን | ንፅፅር | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚዲያን ፎረሞችን መመስረትና ማጠናከር | 2 | 3 | 150 | |
| 3 | የማህበራት፣ ፀረ-ኤድስ ክበባትና ኔትወርኮች አቅም መገንባት (በመሪነት፣ ክበብ አመራር፣ ሜይንስትሪሚንግ፣ በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ኮሙኒኬሽን ርዕሶች ስልጠና መስጠት) | 174 | 364 | 258 | |
| 4 | የአጋርነትና የምክክር መድረክ ፎረሞችን መመስረት/ማጠናከር | 172 | 25 | 152 | |
| 5 | ሀብት የማሰባሰቢያ ፎረሞችን ማቋቋም ማጠናከር | 20 | 21 | 105 | |

- በክልል ደረጃ 7 ፎረሞች እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ ሲሆን 3ቱ በየጊዜው እየተሰባሰቡ እቅዶችን የመደገፍና ስራቸውን የመገምገም ተግባር አከናውነዋል፡፡ እነሱም
    - የመንግስት መ/ቤቶች ፎረም
    - የመያድ ፎረም
    - የከፍተኛ ት/ት ተkሞች ፎረም ናቸው ፡፡

# 4 . የሰው ሃይልና ሌሎች የአስተዳደር ዘርፍ ስራዎች

የአብክመ ኤች አይ ቪ ኤድስ መከ/መቆ/ማስ/ጽ/ቤት በጥቅሉ 558 ሰራተኞች በስራ ገበታ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ሰራተኞች መካከል 218 ወይም 39 በመቶ ሴቶቸ ናቸዉ፡፡ ከአጠቃለይ ሰራተኛዉ 40.3 በመቶ በሰፋፊ ዞኖች ማለትም በሰሜን ጎንደር ሰሜን ሸዋ እና ደቡብ ወሎ ዞኖች

ዉስጥ የሚሰሩ ናቸው። በክልል ደረጃ የሚገኘው የሰራተኛ ብዛት የጠቅላላ ሰራተኛዉን 9.1 በመቶ ብቻ ነው።

በትምህርት ደረጃም አጠቃለይ ሰራተኛዉ ሲታይ 33 በመቶዉ ድግሪና ከዚያ በላይ፣ 60.8% ዲፕሎማ የትምህርት ደረጃ ያላቸዉ ሰሆኑ ቀሪዉ 6 በመቶዉ ከዲፕሎማ በታች የትምህርት ደረጃ እንዳለቸዉ መረጃዎች ያሳያሉ። በ2001 በጀት ዓመት 75 አዲስ ሰራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን 11 ሰራተኞች ደግሞ የደረጃ እድገት አግኝተዋል። ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ የነበሩ 32 ሰራተኞች ደግሞ በገዛ ፈቃዳቸው ከስራ ተሰናብተዋል።

እሰከ 2001 በጀት ዓመት መጠናቀቂያ ድርስ ያለው የሠው ሃይል በዞንና በትምህርት ደረጃ እንደሚከተለው ቀርበል ።

| ተ.ቁ | ዞን/ክልል | የሰው ሀይል | | ድምር | የት/ት ደረጃ | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | | ከዲፕሎማ በታች | ዲፕሎማ | ድግሪና ከዚያ በላይ | |
| 1 | ክልል ማስ/ጽ/ቤት | 34 | 17 | 50 | 10 | 21 | 20 | 51 |
| 2 | ባ/ዳር ልዩ ዞን | 4 | 2 | 6 | 1 | 2 | 3 | 6 |
| 3 | ምዕ/ጎጃም | 30 | 18 | 48 | 1 | 31 | 16 | 48 |
| 4 | ምስ/ጎጃም | 39 | 23 | 62 | 2 | 36 | 24 | 62 |
| 5 | ደ/ጎንደር | 26 | 15 | 41 | | 27 | 14 | 41 |
| 6 | ሰ/ጎንደር | 49 | 27 | 76 | | 56 | 21 | 77 |
| 7 | ሰ/ወሎ | 28 | 17 | 45 | 5 | 19 | 21 | 45 |
| 8 | ደ/ወሎ | 31 | 43 | 74 | 3 | 45 | 26 | 74 |
| 9 | ሰ/ሸዋ | 45 | 29 | 74 | 11 | 45 | 18 | 74 |
| 10 | አዊ | 20 | 14 | 34 | 1 | 16 | 17 | 34 |
| 11 | ኦሮምያ | 14 | 7 | 21 | | 16 | 5 | 21 |
| 12 | ዋግህምራ | 17 | 8 | 25 | | 15 | 10 | 25 |
| | ድምር | 338 | 218 | 556 | 34 | 339 | 185 | 558 |

## 5 . የክትትልና ድጋፍ ተግባራት

ለበጀት ዓመቱ የታቀዱትን ተግባራት ለማሳካት በየደረጃው የክትትልና ድጋፍ ተግባራት ተከናውነዋል። ወቅታዊ የሆነ የመስክ ክትትል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ መፈለግ፣ የስራ አመራርና መደበኛ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ም/ቤት ስብሰባዎች፣ የዕቅድ ክንውን አፈፃፀምን መገምገም የመሳሰሉት መደበኛ የሆኑ የክትትልና ድጋፍ ተግባራት ናቸው።

የክልሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክር ቤት በመስከረም ወር 10ኛ መደበኛ ጉባዔውን ያከሄደ ሲሆን በዚህም ላይ በ9ኛው ጉባዔ የተሰጡ አቅጣጫዎችን በመገምገም፣ የ2000 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም፣ በ2001 ዕቅድ ላይ በመወያየት አቅጣጫ አስቀምጧል። ባሳለፍነው በጀት ዓመት በተለይ በሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻና የህዝብ ንቅናቄ የተገኙት ውጤቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉም ማሳሰቢያ ተሰጥቷል።

የክልሉ ስራ አመራር ቦርድ በክልሉ እየተደረገ ያለውን ሁለገብ እንቅስቃሴ ለመከታተል፣ ውሳኔዎችን ለመስጠትና አቅጣጫ ለማሳየት እንዲሁም ችግሮችን ለመፍታት በፕሮግራሙ መሠረት 13 መደበኛ አስቸኳይ ስብሰባዎችን አካሂዷል። በክልል ደረጃ ከወረዳ ጀምሮ ሁሉንም አጋር አካላት ባሳተፈ መልኩ የክልሉ ስራ አመራር ቦርድ እንዲመራው በማድረግ የ2001 የ6 ወር ስራ አፈፃፀም በደሴና በጎንደር ከተማ የምስራቅና የምዕራብ አማራን በመከፋፈል እንዲገመገም ተደርጓል።ከዚህ በተጨማሪ 9 ወር ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማና የ2002 ዓ.ም የዕቅድ ማዕቀፍ ትዉዉቅ የምስራቅ አማራ በወልድያ ከተማ የምዕራብ አማራ በባህር ዳር ተካሄዷል። በክልል ደረጃ ለሚቀረቡ ፕሮጀክቶችም አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የስራ አመራር ቦርዱ የሰየመው የሪቪው ቦርዱ በጋራ በመሆን ፕሮጀክቶችን እየገመገመ ድጋፍ አድርጓል። ለሴክተሮችና ለሌሎች ፈፃሚዎች የሚያደርገውን የበጀት ድጋፎች ከተለያዩ የሴክተር መ/ቤት በተውጣጡ የሪቪው ቦርድ ኮሚቴ እያፀደቀ ፍትሃዊነቱን ይከታተላል። በዚህም መሠረት 10 ስብሰባዎችን በማድረግ ለ39 ፕሮጀክቶች ምላሽ ሰጥቷል። በክልል ደረጃም የሁሉንም ቢሮዎች በመያዝ የ2000 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ የተከናወነ ሲሆን የ2001 በጀት ዓመት ዕቅድም ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

በዞንና በወረዳ እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በመገምገም በኩል በዞንና በወረዳ መደበኛ የምክር ቤት ጉባዔዎች ተካሂደዋል። በዚህም መሠረት በአመራሩ ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ተደርጓል።

ድጋፋዊ የመስክ ጉብኝት ከክልል ከዞንና ከወረዳ በየወቅቱ እየተደረገ ሲሆን የዞን ማስ/ጽ/ቤቶች እንደየዞናቸው ስፋትና የወረዳዎች ብዛት ተንቀሳቅሰው ለወረዳ ማስ/ጽ/ቤቶችና ለፈፃሚዎች ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ወረዳዎችም በተመሳሳይ መልኩ በቀበሌዎች በመንቀሳቀስ ድጋፋዊ ክትትል አድርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት ግብረ-መልስ እንዲያገኙና አፈፃፀማቸውን እንዲያሻሽሉ አስተዋፀኦ አድርጓል፡፡

በክልሉ ወደ ዞኖችና ወረዳዎች የተደረገን የመስክ ድጋፋዊ ክትትልን በሚመለከት የተለያዩ ኘሮግራሞችን ለማስተባበርና ክትትል ለማድረግ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹም በዞኖች የዕቅድ ክንውን ግምገማዎችና የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ም/ቤት መደበኛ ጉባዔዎች ላይ መገኘትና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገኙበታል፡፡ የክልሉ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ስራን እንደገና በማደራጀት ባስቀመጠው ዕቅድ መሠረት በክልሉ ካሉ ውረዳዎች ውስጥ 30 በመቶ እና ሁሉንም ዞኖች በሶስት ቡድን በመከፋፈል በ6 ወርና በዓመቱ ማገባደጃ ሁለት ግዜ ከክልልና ከዞን በተዉጣጣ ቡድን ድጋፍ ክትትል ተደርጓል፡፡

በሁሉም መስኮች እየተደረጉ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርቶች በየደረጃው በማዘጋጀትና በመወያየት ጠንካራ ተሞክሮዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ክፍተቶች ደግሞ በተቻለ ፍጥነት በየደረጃው እንዲፈቱ ተደርጓል፡፡ መደበኛ የልማትና መልካም አስተዳደር የእቅድ አፈፃፀም በየደረጃው ሲገመገምም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አንዱ ጉዳይ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወደ ክልላችን የሚገቡ አዳዲስ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ማካተታቸውን የሶስትዮሽ ተፈራራሚ በመሆን ክትትል ይደረጋል፡፡

የክትትልና ድጋፍ ተግባሩን ለማጠናከር በየደረጃው የተቋቋሙ የትብብር ፎረሞች እንዲጠናከሩ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በክልል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በኩል ኤች.ኤ.ቪ/ኤድስ በክልሉ ሠራተኞች ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት በተመለከተ ጥናት አድርጓል፡፡በባህር ዳርና በጎነደር ከተሞች ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ በመከላከል የዳሰሳ ጥናት ተደርጓል፣ በዋናው ኦዲተር መ/ቤት በኩል በ2001 የሴክተር መ/ቤቶች ለኤች.አይ.ቨ/ኤድስ እቅድ ከመንግስት በጀት 2% መያዛቸውን ከመደበኛው የኦዲት ስራዎች ጋር በማቀናጀት ኦዲት አድርጓል፡፡ ውጤቱም አብዛኞቹ በጀት እንዳልያዙና አጠቃቀሙ ላይም ችግሮች እንዳሉ ያሳያል፡፡

## 6 . የበጀት አጠቃቀምና በፋይናንስ ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት

**የ2001 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀምንና በፋይናንስ ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራትን በሚመለከት ከለጋሾች የተገኘ በጀት፣ ለፈፃሚ አካላት የተላለፈና ስራ ላይ የዋለ፣ የበጀት አጠቃቀም በዋና ዋና ኘሮግራሞችና በረጂ ድርጅቶች በሚከተሉት ሠንጠረዦች ቀርቧል፡፡**

**በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ ብር 193,136,321.60 ከተለያዩ ምንጮች የተገኘ ሲሆን** *159,255,096.83* **ብር ለተለያዩ ፕሮግራሞችና ተግባራት አፈፃፀም ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህም በበጀት አጠቃቀም** 82.5% **ይሆናል፡፡**

**በአብክመ. ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከ/መቆ ማስ/ጽ/ቤት**

**<u>በ 2001 በጀት ዓመት የተንቀሳቀሰ ገንዘብ በበጀት ምንጭ ( በብር)</u>**

| የበጀት ምንጭ | ካለፈው ዓመት የዞረ ከፈፃሚዎች ተሰብሳቢ | ካለፈው በጀት ዓመት የዞረ ጥሬ ገንዘብ | በበጀት ዓመቱ ከለጋሽ ድርጅቶች የተላከ | በበጀት ዓመቱ የተንቀሳቀሰ ጠቅላላ ገንዘብ | በበጀት ዓመቱ ለዞን ማስ/ጽ/ቤቶች እና ለፈፃሚ አካላት የተላከ | ከፈፃሚ አካላት የተወራረደ /ስራ ላይ የዋለ/* | ከዞን ማስ/ጽ/ቤቶች እና ለፈፃሚ አካላት ያልተወራረደ | በቀጣዩ በጀት ዓመት ስራ ላይ ሊውል የሚችል በባንክ ያለ ገንዘብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግሎባል ፈንድ | 71,601,798.76 | 3,434,352.08 | 68,855,690.07 | 143,891,840.91 | 52,267,983.40 | 82,308,656.15 | 41,561,126.01 | 20,022,058.75 |
| ዓለም ባንክ | 6,311,446.10 | 3,159,039.06 | 21,761,788.61 | 31,232,273.77 | 20,441,058.33 | 25,169,007.63 | 1,583,496.80 | 4,479,769.34 |
| ዩንዳፍ ፕሮጀክት | 399,662.92 | 59,012.19 | 5,155,538.97 | 5,614,214.08 | 3,893,312.87 | 3,667,574.19 | 625,401.60 | 1,321,238.29 |
| ኖራድ ፕሮጀክት | - | - | 7,771,745.95 | 7,771,745.95 | 2,331,444.88 | 1,933,101.08 | 398,343.80 | 5,440,301.07 |
| ሲዲሲ | 187,200.00 | 114,661.95 | - | 301,861.95 | 46,024.48 | 233,224.48 | - | 68,637.47 |
| አክሽን ኤይድ | 154,058.30 | 454,356.60 | - | 608,414.90 | 452,175.61 | 160,393.84 | 445,840.07 | 2,180.99 |
| ዩኤንዲፒ/ዩ ኤን ኤፍ ፒኤ | - | 139,683.26 | | 139,683.26 | 88,599.43 | 4,288.90 | 84,310.53 | 51,083.83 |
| ዩኤንፍፒኤ - ጌትስ ፈንድ | - | - | 321,609.50 | 321,609.50 | 321,609.50 | - | 321,609.50 | - |
| ዩኤንኤፍፒኤ - ለክልላዊ ኮንፈርንስ | - | - | 503,554.29 | 503,554.29 | - | 503.554.29 | - | - |
| ዩኤንኤፍፒኤ - ያለዕድሜ ጋብቻና ኤች.አይ.ቪ. | - | - | 366,365.00 | 366,365.00 | - | 366,365.00 | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ኤድስ** | | | | | | | | |
| **ዩኒሴፍ - ለክልላዊ ኮንፈርንስ** | - | - | 111,138.57 | 111,138.57 | - | 111,138.57 | - | - |
| **ብርቱኬት** | 17,474.00 | - | - | 17,474.00 | 1,400.00 | 18,874.00 | - | - |
| **ፒኤስ አይ** | - | - | 167,685.00 | 167,685.00 | | | | |
| **ፑልድ ፈንድ** | - | - | 1,826,115.74 | 1,826,115.74 | - | - | | 1,826,115.74 |
| **ኢንትራ ሄልዝ/ኢንተርናሽናል** | - | - | 262,344.68 | 262,344.68 | - | 262,344.68 | - | - |
| **አይቴክ/ኢትዮጵያ** | - | - | | - | - | | | |
| **ድምር** | **78,671,640.08** | **7,361,105.14** | **107,103,576.38** | **193,136,321.60** | **79,843,608.50** | **114,234,968.52** | **45,020,128.31** | **33,211,385.48** |
| | | * የተወራረደ ወይም ስራ ላይ የዋለ የሚለው በሰነድ ወይም በ SOE report ከተወራረደው በተጨማሪ ወደ ባንክ ተመላሽ የተደረገውንም ይጨምራል | | | | | | |

# 7 . ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

## 7.1 ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

**በፈፃሚ አካላት በኩል**

- በጀት በወቅቱ ተጠቅሞ አለማወራረድ፣
- የመንግስት ተቋማት ለስራው ትኩረት አለመስጠት፣የ2 በመቶና ኤድስ ፈንድ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ዝቅተኛ መሆን
- ፈፃሚ አካላት ጥራቱን የጠበቀና በወቅቱ ሪፖርት መላክ አለመቻል፣
- የማህበረሰብ ውይይት ጣቢያዎችን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የታቀደውን ያህል መፈፀም ያለመቻል፤ አጋር አካላት በቂ ድጋፍ አለማድረግ፣
- ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሠዎች ዘላቂ የሆነ ድጋፍ አለማድረግ፣ የማህበር አባላትም አለመስማማት
- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የማህበረሰብ ውይይቱን በተገቢው መንገድ አለመምራት
- በቀበሌ ደረጃ ያለው የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አደረጃጀት አለመጠናከር
- በአጠቃላይ ቅንጅታዊ አሰራር አለመጠናከር

**በማስተባበሪያ ጽቤቱ በኩል**

- የፀረ-ኤድስ ዘመቻውን በታቀደው መሠረት ለማከናወን የበጀትና የቁሳቁስ እጥረት ማጋጠሙና በአንዳንድ አካባቢዎች አገልግሎቱ መቆራረጥ
- ከክልል በጀት በወቅቱ አለመላክ
- በተወሰኑ ዞኖችና በበርካታ ወረዳዎች የተሽከርካሪ ችግር መኖር
- የሪፖርት ጥራት ማነስ ( በወቅቱ ያለመላክ፣ ወጥ አለመሆን፣ ተከታታይ አለመሆን፣ድግግሞሽ ያለው መሆኑ)
- ቅንጅተዊ አሰራር እንዲኖር አለማድረግ

## 7.2 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- የተላከውን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ አውሎ ሂሣቡን እንዲወራረድ ለዞን አስተዳደር፣ ለሴክተሮች ማሳሰቢያ ተሰጧል፣
- የዞን ማስ/ጽ/ቤቶች በተቻለ አቅም ለወረዳዎች ክትትልና ድጋፍ እንዲያደርጉ፣ በክልል ደረጃ ለየፕሮግራሞቹ ለዞኖች ገለፃ ማድረግ፣ የዕለት ከዕለት የስልክ ግንኙነት በማድረግ መወያየት :
- በመስክ ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ የነበሩ ችግሮችን መፍታት፣
- በግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በማካሄድ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ መፍትሄ መስጠት
- ከፌዴራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት እና ከሌሎች ረጅ ድርጅቶች ጋር በመነጋገር ለዕቅድ ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት ማግኘት፣
- የምርመራ የአቅርቦት ችግር ከጤና ጥበቃ፣ከፌደራል ጋር በመወያዬት ለመፍታተት ተሞክሯል

# 8 . የታዩ መልካም የስራ እቅስቃሴዎች

- በየደረጃው ያለው አመራር በሚፈለገው ደረጃ ባይሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ትኩረቱ እየጨመረ መምጣት
- በዞንና በወረዳ በሴክተሮች አፈፃፀም ውድድር HIV/AIDS አንድ የማወዳደሪያ መስፈርት መሆኑ
- የህብረተሰቡ ግንዛቤ ማደግና በየዘርፉ አገልግሎት በማግኘትም ሆነ ምላሽ በመስጠት እያሳየ ያለው እንቅስቃሴ የሚያበረታታ መሆኑ
- በድጋፍና ክብካቤ ተግባራት የማህበራት ተሳትፎ ማደግ፣እየተከናወኑ ያሉ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ውጤታማነት እየተሻሻለ መምጣት
- በኤድስ ፈንድ ወደ ተግባር በመገባት መጀመሩና ወላጅ ያጡ ህጻናት ቋሚ የሆነ የምግብና የትምህርት እድልና ድጋፍ ማግኘታቸው፣
- የህዝብ ንቅናቄ ተግባራት ተጠናክረው መቀጠል፣
    - o የማህበረሰብ ውይይቶች ወደ ዕድር መቀየር፣ በድጋፍና እንክብካቤ መሰማራት፣ የተወሰኑ ውሳኔዎች ተግባራዊ መደረግ፣ህብረተሰቡ የአካባቢውን ችግር በራሱ ለመፍታት መሞከሩ፣በልማት ስራ መሰማራት፣

o የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ እንቅስቃሴ እየተሻሻለ መምጣት

- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የጤና አገልግሎቶች እየተስፋፉ መምጣት፣
- ከአጋርና ረጂ ድርጅቶች ጋር ያለው ትብብርና የኘሮግራሞች አፈፃፀም መሻሻልና የአጋር ድጅቶች ከክልሉ ጋር ለመስራት ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ መሆን፣

## 9 . ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- ተከታታይና መደበኛ የሆነ ድጋፋዊ ክትትል ማካሄድ፣ ለዚህም በየደረጃው ያለው ፈፃሚ አካል ተጠሪ ከመመደብ ያለፈ ትርጉም ያለው ስራ ከተልዕኮአቸው አንፃር አካተው እንዲሰሩ በማድረግ፣
- በየደረጃው ያለው የኤችአይቪ/ኤድስ ምክር ቤትም ሆነ ስራ አመራር ቦርድ/ኮሚቴ በፕሮግራሙ መሠረት እንቅስቃሴውን እንዲገመግም፣ አቅጣጫ እንዲሰጥ በማድረግ
- የመንግስት፣መንግስታዊ ያልሆኑ፣የሐይማኖት ድርጅቶችን፣የሲቪክ ማህበራትን እንቅስቃሴ የበለጠ ማቀናጀት
- ለሁሉም ፕሮግራሞቻችን አፈፃፀም ግብዓት የሆነውን የማህበረሰብ ውይይት ጠንካራ ክትትል በማድረግ የተጀመሩት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ ባልተጀመረባቸው ቀበሌዎች አዳዲሶች እንዲጀመሩ እንዲሁም ተጋላጭ የሆነውን ወጣት ህብረተሰብ በት/ት ቤት ለማግኘት በእነሱም አማካኝነት ለቤተሰቦቻቸው ለማዳረስ የትምህርት ቤት የማህበረሰብ ውይይት አጠናክሮ ማስቀጠል
- የ2002 ዕቅድ ከቀበሌ በመጀመር ማሳቀድ፣እቅድ ሲታቀድና ሲተገበር በበለጠ ተጋላጭ በሆኑ የህ/ሰብ ክፍሎች( ሴቶች፣ወጣቶች፣ሴተኛ አዳሪዎች ፣ተማሪዎችና ተንቀሳቃሽ ሰራተኞች የመሳሰሉት) እና በመከላከል ላይ ትኩረት ማደረግ
- ለኤች.አይቪ/ኤድስ ምላሽ ከውጭ ልዩ ልዩ ምንጮች ይልቅ በአካባቢ ሃብት ላይ ትኩረት በማደረግ ምላሹን ዘላቂ ማድረግ
- ለተለያዩ ኘሮግራሞች የመጣን በጀት በወቅቱ ስራ ላይ አውሎ በማወራረድ አፈፃፀምን ማሳደግ፣
- በድጋፍና እንክብካቤ ላይ የሚውለውን የውጭም ሆነ የአካባቢ ሃብት ዘላቂ በሆኑ በተለይም በገቢ ማስገኛ ላይ እንዲውል፣ እንዲሁም

ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሠዎች የመስራት ባህልን እንዲለምዱ ማድረግ፣ በተጨማሪም በማህበራት አባላት መካከል ያለውን አለመግባባት ትኩረት ሰጥቶ መከታተልና መፍታት

- ከረጂና አጋር ድርጅቶች ጋር ይበልጥ ተቀራርቦ መስራት፣
- በክልል፣ በዞን በወረዳ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን መረጃ በተደራጀ መንገድ መያዝ፣ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ የሪፖርት ልውውጥ ማድረግ፣
- የዞንና የወረዳ ማስ/ጽ/ቤቶችንና ባለሞያዎች አቅም የማጎልበት ስራ አጠናክሮ መቀጠል፣
- የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የሙከራ ትግበራውን ከክልል እስከ ወረዳ ተግባራዊ በማድረግ ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት